## ስለ ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሐትቺንግስ (Gregory C. Hutchings, Jr.)

ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ. ሐትቺንግስ ጁኔር የቲ.ሲ. ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ'95 ተመራቂ ናቸው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በፓትሪክ ሔንሪ፣ ጃሜስ ኬ.ፖልክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ማውንት ቨርነን የኪሚዩኒቲ ት/ቤት፣ ዊሊያም ራምሴ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ከዚያም በፍራንሲስ ሲ. ሐመንድ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትለዋል።

እንደ ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሩጫ ቡድን አባል፣ የአሜሪካ መጪው የቢዝነስ መሪዎች ክለብ እንዲሁም የቲ.ሲ.ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የክፍሉ ሲኒየር ምክትል ፕሬዘደንት እና የፐሮም ኪንግ ነበሩ!

ሱፐር ኢንቴደንት ከመሆናቸው ቀደም ሲል ዶ/ር ሐትቺንግስ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የቅድመ-መዋእለ ሕጻናት መርሃግብር እና የመካከለኛ ትምህርት ፕሮግራም ዳይሬክተር በመሆን ሰርተዋል። የኢንተርናሽናል ባካሎሬት (IB) ፕሮግራም የእጪነት ስራ ያስጀመሩ ሲሆን ከዚያም በጀፈርሰን ሒዊስተን ትምህርት ቤት በስራ እንዲውል ተደርጎል እንዲሁም አዲስ የመካከለኛ ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እንዲጀመር አስደርገዋል። ከ2013 እስከ 2018 ባለው ጊዜ በኦሃዮ ስቴት ክሌቭላንድ ከተማ ወጣ ብሎ ባለው የሼከር ሐይት ትምህርት ቤቶች (Shaker Heights Schools) ሱፐር ኢንቴንደንት (ዋና ስራ አስኪያጅ) በመሆን ስርተዋል። በ2018 ወደ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በሱፐር ኢንቴንደንትነት ተመልሰዋል።

ከፍተኛ ልምድ ያለቸው የትምህርት ባለሞያና አስተዳዳሪ ዶ/ር ሐትቺንግስ እንደ አስተማሪ፣ ረዳት ርእሰ መምህርና በመካከለኛ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ቤት ርእሰ መምህርነት አገልግለዋል። የማስተማር ስራ በማናሰስ ከተማ ፒሪንስ ዊሊያም ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤት የጀመረ ሲሆን ከዚያም በሪችመንድ ከተማ አጠገብ በቸስተርፌልድ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤት እና በናሽቪል የህዝብ ትምህርት ቤት በቴኔሲ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማህበር የተማሪዎችን ውጤት እንዲያድግ አስተዋፆ በማድረጋቸው እንዲሁም ውጤታማ ስራ በማከናወን በናሽቪል ሜትሮፖሊታን ካሉ መካከለኛ ትምህርት ቤት አንደኛ በመሆን የቴኔሲ መካከለኛ ትምህርት ቤት የዓመቱ ታዋቂ ርእሰ መምህር የሚል ስያሜ አግኝተዋል።

ዶ/ር ሐትቺንግስ የተለያዮ የሙያ ዘርፍ ጥናት የባችለር ዲግሪ ከኦልድ ዶሚዩኒየን ዮኒቨርስቲ፣ በትምህርት አመራር ማስተርስ ዲግሪ ከጆርጅ ሜሰን ዮኒቨርስቲ እና በትምህርት ፖሊሲ፣ እቅድ አወጣጥና አመራር ከዊሊያም እና ሜሪ ኮሌጅ የዶክትሬት ዲግሪ ተቀብለዋል። የእርሳቸው እና የባለቤቱ ቻርሊ ሁለት ለትምህርት የደረሱ ልጆች በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ይከታተላሉ።